"ስነፅሁፍ የሌለው ህዝብ ባህል የለውም፤ ባህል የሌለው ህዝብ ደግሞ አንድነት የለውም:: በዚህም የተነሳ ነፃነቱን ያጣል"

አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ፤ አልቦ ዘመድ

አምስተኛ ዕትም
ቅዳሜ ግንቦት 21/2013 ዓ.ም
በየሁለት ሳምንቱ ለህትመት የሚበቃ

ሀገር አማን

ሀገር አማን በደመራ ሚድያና ኮሚዩኒኬሽን የምትዘጋጅና በየ15 ቀኑ የምትወጣ በነፃ የምትታደል 'ሚኒ ሜጋዚን' ስትሆን፤ በከተማችን፣ ብሎም በአገራችን ዙሪያ በሚያጋጥሙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በዋናነት ታተኩራለች። በሀገር አማን ኤዲቶርያል ላይ ከሚወጡ ሀሳቦች በቀር ሌሎቹ በሙሉ የፀሀፊዎቹን አቋም እንጂ የመፅሄቷን፣ ወይንም የደመራ ሚድያና ኮሚዩኒኬሽንን አቋም አያንፀባርቁም። ሃሳብ፣ ጥያቄ አስተያየት ካሎት፤ ወይንም ሀገር አማን ላይ ፅሁፍዎን ለመላክ ከፈለጉ፣ ከስር ባሉት አድራሻዎቻችን ያገኙናል። መልካም ንባብ!

Demera Media & Communication Service PLC
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
+251 911 057837 +251 911 488888

@demeramedia1
Demera Media and Communication
demeramedia1@gmail.com
Demera Media
www.demeramedia.com

© www.bridalmusings.com

ስለ ትዳር

(ጌቱ ከበደ ኪዳኔ - የኢንጅነሪንግ እና ማኔጅመንት ባለሞያ)

ለመሆኑ ትዳር እንዴት ነው?

ትዳር ለአንዳንዶች ምቾት ነው፤ ለአንዳንዶች ደግሞ ስቃይ። ትዳር እንደ ሁኔታው ነው። ትዳር ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም። የላጤ ኑሮም አንድ ዓይነት አይደለም። ለነገሩ ሁሉም ኑሮ አንድ እንዲሆን አይጠበቅም።

ከጉርምስና ጀምሮ የሚገርመኝ የስኬታማ ህይወት ጉዞ ወሬ አንድ ዓይነት ዲዛይን ነገር ነበር። መማር፣ ኮሌጅ መግባትና መመረቅ፣ ሥራ መያዝ፣ ቤት መሥራትና ማደራጀት፣ ማግባት፣ ልጅ መውለድ፣ ልጅን አስተምሮ ማስመረቅና መዳር በቃ። ትክክለኛ እና ስኬታማ የህይወት አካሄድ ይህ ነው የሚል ነገር እሰማ ነበርና ለምን የግድ እንዲህ ይሆናል? እል ነበር።

ሳይማሩ ሥራ መያዝ፣ ሳያገቡ መኖር፣ ቤት ሳይሠሩ መኖር ለምን ከስኬት ያነሰ ኑሮ ተደርጎ ይቆጠራል? ብዬ አስብ ነበር።

ለመሆኑ ትዳር ለምን ይያዛል?

የተለያዩ ሰዎች ትዳር የያዙበት ምክንያት የተለያየ ነው። ለፍቅር፣ ለጾታዊ ፍላጎት እርካታ፣ በኑሮ ለመረዳዳት፣ ለልጅ ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው።

ከሃይማኖት እና ሞራል መርሖች ውጪ፣ ልጅ ለማግኘት ሲባል ማግባት ግዴታ አይደለም። ነገር ግን በትዳር ውስጥ ሆኖ መውለድ፣ ለሚወለደው ልጅ ስነ-ልቦና እና አስተዳደግ የተሻለ ነው - በርግጥ exceptions እንዳሉ ሳይረሳ። ልጅ ለማግኘት የሚጋቡ፣ ልጅ ካልተገኘ ይፋታሉ። ትዳር በልጅ ሊዋብ ይችላል እንጂ ትዳር የልጅ ማምረቻ ፋብሪካ ግን አይደለም። አግብተው በፈቃዳቸው ልጅ መውለድ የማይፈልጉ ባለትዳሮች አሉ - በተለይ በጀርመን ብዙ እንዳሉ አንብቤያለሁ።

በትዳር እንጂ ከትዳር ውጪ ልጅን አለመውለድ ከራስ አብልጦ ለልጅ ፍቅርንና ኃላፊነትን ማሳያ ነው።

በኑሮ ለመረዳዳት ብሎ ትዳር መያዝ ዓይነቱ ሁለት ነው። አንዱ በሃሳብ፣ በጊዜና በጉልበት ለመረዳዳት ሌላው በኢኮኖሚ። የጊዜ፣ የሃሳብ እና የጉልበት መረዳዳቱ በተለይ ባላደጉ ሀገራት የኑሮ ኡንሹራንስ ነው።

የኢኮኖሚው ግን የኢኮኖሚ ዓቅም ሲጠናከር ትዳሩ ችግር ላይ ሊወድቅ ይችላል። "ሀብት በበር ሲገባ ትዳር በመስኮት ይወጣል" የሚሉት አባባል ዝም ብሎ የመጣ አይደለም። ለኢኮኖሚ ችግር ተብሎ አድፍጦ በትዕግስት የተቀመጠ ባለትዳር፣ ዓቅሙ ሲፈረጥም "ዞር በል/ ዞር በይ" ሲባባሉ አይተናል። የጾታዊ ግንኙነት እንኳን ከትዳር ውጪ እንደሚታሰበው አይደለም። በወንድና በሴት በኩል ያለው ፍላጎትም አንድ ዓይነት አይደለም። በተለይ ልጅ ከተወለደ በኋላ በሴቷ በኩል የሚታየው የፍላጎት መቀነስ ብዙ ወንዶች ሲበሳጩበት የሚሰማ ነው። ያንን በጊዜ መረዳት ጠቃሚ ነው።

በባህሪይም በኩል ቢሆን ከትዳር በፊት የሚታይ ባህሪይ እና በትዳር ውስጥ የሚታይ ባህሪይ አንድ ላይሆን ይችላል። በዚህ ላይ የሚነገር አንድ አባባል አለ። ሴቷ ከትዳር በፊት ወንዱ ላይ የሚታዩትን መጥፎ ባህሪያት አስቀይረዋለሁ በሚል እሳቤ ወደ ትዳር ትገባለች። ወንዱም ከትዳር በፊት የሚያያቸውን የሴቷን ትህትና እና እንክብካቤ አይቀየሩም ብሎ በመተማመን ወደ ትዳር ይገባል።

ሁለቱም ግን ተሳስተዋል - የሴቷ ባህሪይ ይቀየራል፣ የወንዱ ደግሞ አይቀየርም። የወንድ ባህሪይ ባለበት ሲቀጥል፣ የሴቷ ደግሞ ይቀያያራል። ይሄ ተፈጥሮ ነው። እኔ በበኩሌ ለትዳር መያዝ አሳማኝ ሆኖ ያገኘሁት Banco የተሰኘው የ Papillon ተከታይ መጽሓፍ ላይ ያነበብኩት ሃሳብ ነው። ሃሳቡ በጥቅሉ እንዲህ የሚል ነው።

ሃሳቡ ሁለት ጥንዶች አብረው ውለውም አድረውም ሲለያዩ ወድያው የሚነፋፈቁ ከሆነ ወይም መለያየት ካቃታቸው ያን ጊዜ እነዚህ ሰዎች በአንድ ጣርያ ስር መኖር አለባቸው የሚል ነው።

ይህ ደግሞ የሚመጣው ልዩ ፍቅር ሲኖር ነው።

ስንቱ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ አጋጥሞት አግብቶ እንደሆን አላውቅም። እንደዚያ ለመሆን በጨዋታና በቁም-ነገር መግባባት፣ መተሳሰብ፣ መከባበር፣ መተማመን፣ መቻቻል፣ ይቅር መባባል እና መሸናነፍ መቻል ጠቃሚ መሠረቶች ናቸው። እንዲያም ሆኖ ግን ትዳር ሁልጊዜ አልጋ ባልጋ አይደለም። በየጊዜው የራሱን ፈተና ብቅ እያደረገ ይፈትናል። ቁም-ነገሩ ፈተናውን በጥበብ መወጣት ላይ ነው፣ ከትንሽ ነገር ትልቅ ጥል አለመፍጠር ላይ ነው። በመከባበር ልዩነትን መፍታት ነው።

ትዳር አንድ ተቋም ቢሆንም የሁለት የተለያየ አስተዳደግ፣ አስተሳሰብ እና የህይወት ግብ ያላቸው ሰዎች ጥምረት መሆኑን ተረድቶ በጋራ ግብ፣ ኃላፊነቶች እና ጉዳዮች ላይ አብሮ መተጋገዝ፤ ለግላዊ ጉዳዮች እና ግቦች ደግሞ ቦታ በመስጠት አብሮ መኖር መቻል ትዳሩን ውብና ምቹ ያደርገዋል።
ትዳር ውብና ምቹ ሲሆን ደግሞ ዓለም የምታምርና ደማቅ ብርሃን ሆና ትታያለች። ነገሮች ሁሉ በየቦታው ስክት ስክትክት ይላሉ ልክ እንደ ዶሚኖ። ትዳር ሲናድም እንደዚያው ልክ እንደ ዶሚኖ ብዙ ነገር አከታትሎ ይንዳል።

በትዳር ሲኖር የጋራ ጉዳይና የግል ጉዳይን በሚዛን አቻችሎ መኖር ይጠይቃል። ለሌላኛው ሰው የግል ጉዳይ ቦታ መስጠትና ጣልቃ አለመግባት የአክብሮት መገለጫ ነው።

ትዳር አንድነት ቢሆንም፣ አንድ ዓይነትነት አይደለም እና ተዋደዱ፣ ተፋቀሩ፣ ተከባበሩ፣ ተሳሰቡ በአንድ ኑሩ፤ ግን ደግሞ ልዩነትን አክብሩ።

ላገባችሁ መልካም ትዳር! ሰሞኑን ለምታገቡም መልካም ጋብቻ!

ኮረማሽ የጉዞ ወኪል

ስልክ ቁጥር 0993 949 053

ኮረማሽ - Koremash

ታላቁ ኢትዮጵያዊ የዜማ ሊቅ የቅዱስ ያሬድ ታሪክ

(በአብይ መሃመድ - ሲጅንግ፣ ደቡብ ኮርያ)

ቅዱስ ያሬድ በ505 ዓ/ም በአክሱም ተወለደ። ቅዱስ ያሬድ በተወለደ ገና በ7 ዓመቱ አባቱ ስለሞተ እናቱ ለአጎቱ እንዲያሳድገው እና እንዲያስተምረው አደራ ብላ ሰጠችው። አጎቱ አባ ጌዲዎን በአክሱም ፂዮን የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን መምህር ነበሩ ። አባ ጌዲዎን ህፃን ያሬድን ከእሳቸው ጋር አድርገው ያስተምሩት ነበር። ሆኖም ያሬድ አብረውት ከሚማሩት ተማሪዎች ጋር መወዳደር ባለመቻሉ አባ ጌዲዮን ደጋግመው ይገስፁት እና ይመክሩት ነበር።

ቅዱስ ያሬድ አስተማሪዎቹ የሚሰጡትን ትምህርት ደጋግሞ ቢያጠናም አልገባው እያለ ስለተቸገረ አብረውት የሚማሩት ተማሪዎች ይቀልዱበት እና ያፌዙበት ነበር። የትምህርቱ ነገር ስላልተሳካለት ተስፋ በመቁረጥ ትምህርቱን ትቶ ሌላ ቦታ በመሄድ ህይወቱን ለመኖር ወሰነ።

ከዚያም ያሬድ ከትምህርት ቤት ጠፍቶ ወደ ሌላ ሀገር በመሄድ ላይ ሳለ ከባድ ዝናብ በመዝነቡ ከአንድ ዛፍ ስር መጠለል ግድ ሆነበት በዚያች ዛፍ ስር ተቀምጦ በምን ምክንያት ከጓደኞቹ በታች እንደሆነ ሲያዝን ሲተክዝ ቆየ። በመሀልም አንድ ትል የዛፉን ፍሬ ለመመገብ ፈልጎ ወደላይ እየወጣና እየወደቀ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ ከቆየ በኋላ በሰባተኛዉ ጊዜ ወጥቶ ፍሬዋን ሲመገብ ተመለከተ።

ያሬድም የዚህ ትል ተስፋ አለመቁረጥ ትዕግስቱን ጽናቱን ተመልክቶ "እኔም ተስፋ ሳልቆርጥ ብዙ ጥረት ካደረኩ እንደዚህ ሊሳካልኝ ይችላል"ብሎ ወደ አክሱም ተመልሶ ከአጎቱ ለመማር ወሰነ። ያሬድ የአጎቱን የአባ ጌዲዎንን ምክርና ተግሣጽ ለሕይወቱ የሚጠቅም መሆኑን በመረዳቱ ትምህርቱን በትጋት ቢማርና ቢያጠና ያሰበዉ ደረጃ ለመድረስ እንደሚችል በመገንዘብ ወደ መምህሩ አባጌዲዎን ጉባኤ ቤት ተመለሰ።

ከዚያም አጎቱ ተቀብለው አስተማሩት።ጓደኞቹ እና መምህራኖቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያመጣውን ከፍተኛ እና የማይታሰብ ለውጥ በማየት ተደነቁ። በግምት እድሜው 30 ሲደርስ አምላኩን ለማመስገን ዜማ እንደተገለፀለት ስለእሱ የተፃፉ ድርሳናት የሚያሳዩ ሲሆን ዜማዎቹን በሦስት ዓይነት ድምፅ ማለትም በግእዝ፣ በዕዝል፣ እና በዓራራይ ዜማ ማዘጋጀት ቻለ። ግዕዝ ማለትም አንደኛ በመጀመሪያ የተገኘ ማለት ነው፤ ዕዝል ማለትም ሁለተኛ ሆኖ ከግዕዙ ጋር ተደርቦ፣ ተጨምሮ (ታዝሎ) የሚነገር ማለት ነው። ዓራራይ ማለትም ሦስተኛ ተጨማሪ ሆኖ አራኅራኂ፣ ርኅራኄ/አኅዛኝ ልብን የሚመስጥና ደስ የሚያሰኝ ማለት ነው።

የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች መንፈሳዊ ይዘት ያላቸዉ ናቸዉ ። በድርሰቶቹ የሚታዩት የቃላት አመራረጥ ፣ የዐረፍተ ነገር አወቃቀር ፣ የሚስጥር ፣ የዘይቤ አገላለጥ ቅዱስ ያሬድ ከፍተኛ የስነ-ጽሑፍ ተሰጥኦ እንደነበረዉ ለመረዳት ይቻላል። በቅዱስ ያሬድ የተደረሱት የዜማ መጻሕፍት ድጓ፣ ጾመድጓ፣ ዝማሬ፣ ምሥዋዕትና እና ምዕራፍ ይባላሉ። ቅዱስ ያሬድ ለዜማዎችም ስምንት የሙዚቃ ምልክቶችን በመጠቀም ውብ አድርጎ ቀምሮታል።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ያሬድ ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመንቀሳቀስ ቤተክርስቲያኖችን እያሰራ እና እያስተማረ ቆይቷል ።ከዚህ በኋላ ዜማ፣ ብሉይ ኪዳን፣ አዲስ ኪዳንን እና ቋንቋ ሲያስተምር ከቆየ በኋላ በ571 ዓ/ም ግንቦት 11 ቀን ህይወቱ እንዳለፈ እና እንደተቀበረ መዛግብት ያስረዳሉ። ህይወቱም ካለፈ በኋላ የእርሱ ደቀመዛሙርት ከእርሱ የተማሩትን የዜማ ባሕልና ሥርዓት በሁሉም የሀገሪቷ ክፍሎች እየተዘዋወሩ በየገዳማቱ ሁሉ ስላስተማሩ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት እስከ ዛሬ ድረስ ጸንቶ መኖር ችሏል ።

አበራ ለማ

ደራሲ አበራ ለማ የተወለደው በ1943ዓ.ም. ፍቼ ሰላሌ ውስጥ ነው። እድገቱ ወሊሶንና አዲስ አበባን ያካትታል። ከሃገራችን ገጣሚያንና አጫጭር ልቦለድ ጸሓፊዎች አንዱ ነው። በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ጥናት ከአዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ የማዕርግ ተመራቂ ነው። ሙያው ጋዜጠኝት ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ፕሬስ መምሪያዎች ሠርቷል። ከጦር ግምባር ጋዜጠኝነት እስከ ኪነጥበባት ዘርፎች ሃያሲነት ደርሷል። በጦር ሜዳ ዘገባውም “የጦር ሜዳው ቀሲስ” የሚል ቅፅል ስም ተሰጥቶት ነበር ።

እስከ ሰማኒያዎቹ አጋማሽ ድረስ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ዋና ጸሃፊ ሆኖ አገልግሏል። ዛሬ የኖርዌይ ነዋሪ ነው። በኖርዌይ ደራስያን ማኅበር ብቸኛውና የመጀመሪያው ጥቁር እና በአፍ መፍቻ ቋንቋው የሚጽፍ አባል ደራሲ ነው። በዚህ ማኅበር ውስጥ የዓለም አቀፍ ኮሚቴው የረዥም ዘመን አባል በመሆንም ይታወቃል። ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን እና (1997) ስዊድናዊ/ኤርትራዊ የሆነውን የአስመራውን አስረኛ፣ ደራሲና ጋዜጠኛ ዳዊት ይስሐቅን (2009 እ.ኤ.አ.) ሃሳብን በነጻ የመግለጽ ሽልማት እንዲሸለሙ በእጩነት አቅርቦ ማሸለሙም ይታወሳል።

በደራሲ አበራ ለማ የታተሙ ሥራዎች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

-1967 ኩል ወይስ ጥላሸት፣ የግጥም መድብል፣
-1974 ሽበት፣ የግጥም መድብል፣
-1975 ሕይወትና ሞት፣ የአጫጭር ልብ ወለዶች መድብል፣
-1976 ሞገደኛው ነውጤ፣ ኖቭሌት፣
-1978 አባደፋር፣ ከሌሎች ደራስያን ጋር…ስብስብ፣
- 1978 ጽጌረዳ ብእር፣ ከሌሎች ገጣሚያን ጋር… ስብስብ፣
-1980 የማለዳ ስንቅ፣ ያጫጭር ልቦለዶችና ግጥሞች መድብል፣
-1980 መቆያ፣ ያጫጭር ልቦለዶችና ግጥሞች መድብል፣
-1981 ትዝታን በጸጸት፣ ያጫጭር ልቦለዶች ትርጉም….በጋራ፣
-1994 አውጫጭኝ፣ የግጥም መድብል፣
-1994 ሙያዊ ሙዳዬ ቃላት፣ ኢልቦለድ… የቋንቋ ጉዳይ
-1998 የእውቀት ማኅደር፣ ኢልቦለድ… ጠቅላላ እውቀት፣
-2003 E.C. ULIKE HORIZON Norsk Saksprosa samling med andre forfatterer
-እውነትም እኛ፣ የግጥሞች ስብስብ ቪዲዮ በዲቪዲ፣ ታህሳስ 2003
-ጥሎ ማለፍ፣ ታሪካዊ ልቦለድ፣ ጥር 2003 ዓ.ም.
-ሽፈራው ሞሪንጋ ይገኙበታል ።

ቅርፊቱን መስበር

ቃልኪዳን አምባቸው (ከቡክሳይት - መጽሀፍ መደብር)



የአሁን ማንነትዎ ምቾት ይሰጠዋታል?

በሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በባንኩክ፣ ታይላንድ፣ መንግስት በገጠሩ አካባቢ ትልቅ አውራ ጎዳና ለመዘርጋት ያስባል። ነገር ግን በሚገነባው መስመር የቡዲሂዝም ገዳም ከቤተመቅደስ ጋር ሰፍሯል። ስለዚህም ገዳሙን ከፍተኛ ክብደትና አስራ አንድ ያልህ ጫማ ቁመት ኖሮት በሸክላ ከተሰራው የቡድሃ ሃውልት ጋር አብሮ ወደ ሌላ ስፍራ ማጓጓዝ ያስፈልግ ነበር። እና የመንግስት ሠራተኞች የኮንስትራክሽን ማሽኖች እየተጠቀሙ ገዳሙን ክፍል በክፍል ወደ ሌላ ስፍራ መውሰድ ጀመሩ። ሠራተኞቹ የቡድሃን ሃውልት ወደ አዲሱ ስፍራ እያጓጓዙ ሳሉ፤ ሃውልቱ ላይ ያለው ሸክላ እየተናደ መውደቅ ጀመረ። በዚህ ጊዜም ሕዝቡ የከበረ የሐይማኖቱ ምልክት በመሆኑ ተደናገጠ። ሠራተኞቹ ይበልጥ ለማዘዋወርም በተጉ ቁጥር፣ ሸክላው እየተደረመሰ ሄዶ ሙሉ በሙሉ ወደቀ። ወዲያውኑም ሠራተኞቹ ባዩት ነገር ተደመሙ። ሸክላው ሙሉ ለሙሉ ከፈረሰ በኋላ አንዳች ያልታሰበ ነገር ተገለጠ፡- ሃውልቱ ከውስጡ ሙሉውን ንጹህ ወርቅ ነው። ሃውልቱን የማንሳት እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት፣ ሕዝቡ ሃምሳ ሺ ዶላር ያህል ዋጋ እንዳለው ይተምን ነበር።

ዛሬ፣ ወርቃማው የቡድሃ ሃውልት በሚሊዮን በሚቆጠር ገንዘብ የሚተመን ሲሆን፣ ካለውም ታሪክ የተነሳ በየአመቱ በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ ጎብኚዎች ይታያል። ጭብጡ የሚያሻማ አይደለም። የሚታየን የላይ የላይ ገጽታና ነባራዊ ሁኔታ የግድ ተጨባጭ እውነታውን እያንፀባርቅም። አሁን ያለን ሕይወት ትክክለኛውን ማንነታችንን አይወክልም። ሸክላው በንፁህ ወርቅ የተሠራውን ሃውልት እንደሸፈነው፣ እያንዳንዳችን ውስጥ ያለው “ወርቅም” መገለጥን ይጠባበቃል። ይኸም ወርቅ፣ ወሰን አልባ ስኬት፣ ከፍተኛ ልቀት፣ የውስጥ ሙሉነት፣ መላበስ የምንሻው ማራኪ ስብዕና ነው። እርስዎ ሊያደርጉት የሚገባው እውነተኛውን ማንነትዎን ያገኙ ዘንድ ሸሉን በመግፋት እውነተኛ ስብዕናዎን መግለፅ ነው።

ቅርፊቱን እንስበረው

አብዛኛዎቻችን ኑሯአችን ቅርፊት ውስጥ ነው። ውስጡ ድቅድቅ ጨለማና አቧራ ቢሆንም ከዚያ ማፈትለክና መውጣት እንደማንችል እናስባለን። ስለ ቅርፊቱ ለገዛ ራሳችን የምንነግረው ታሪክ አለ፤ ታሪኩ ግን ሐሰተኛና የተወናበደ ታሪክ ነው። እውነት መስሎም የሚሰማን ተደጋግሞ ስለሰማነው ብቻ ነው።

ከቆረጥን ግን ቅርፊቱን መስበር እንችላለን። ገደቡን ጥሰን በመውጣት የደማቁን አለም ብርሃን ማየት ይቻለናል። መቅዘፍን፣ መብረቅን መማር ይቻላል። ቅርፊቱ ስብዕና በመባል ይታወቃል። አብዛኛው ሰው ልቆ መሄድ እንደሚችል ሳይገነዘብ በሚገታው ስብዕናው ውስጥ ዕድሜውን ሙሉ ተከርችሞ ይኖራል። እንዲህ ያሉ ሰዎች ራሳቸው በፈለሰፉት ውስን “ማንነት” የተጠቁ ናቸው።

በማለዳ የሚነሱት ጭጋጋማና አቧራ በሆነው አለም ውስጥ ነው። የብርሃን ጭላንጭል እንኳ አይታያቸውም። ጠርዘ የያዛቸውን ውስጣዊ ቅርፊት መግፋትና ሰብሮ መውጣት ተስኗቸዋል። በጭለማው ዙሪያ ከትመው ኑሯቸውን ያለምችት ይገፋሉ።

ያስታውሱ ከማህፀን አለም ተገፍተው የወጡት በተፈጥሮ ኃይል ነበር። አሁን ግን ከዚህ የድንግዝግዝ ስብዕና ቅርፊት በመስበር መውጣት የሚችሉት በራስዎ ኃይል ነው። ለዚህ የሚያበቃ ገደብ የለሽ ሃይል ደግሞ ውስጥዎ አለ።

ሰዎች ይሄ ኃይል ወዴት አለ? ሲሉ ይደመጣሉ ወይንም ኃይሉ ውስጣቸው እንዳለ አይሰማቸውም። እናም ሳያቋርጡ ቅርፊቱን ከመግፋት ይልቅ አቅመቢስነታቸውን መቀበሉ ይቀናቸዋል። ታዋቂ የስኬት ሰው አርኖልድ ቤኔት ለዚህ የሚያረካ መልስ አላቸው። ገደብ የለሽ ኃይል ውስጥዎ እንደተከመረ ያስረዳሉ።

‹‹ እገዛ ራስዎ ውስጥ ኃይል ለመፍጠር እየተመኙ ይሆናል። ሆኖም ኃይልን እገዛ ራስዎ ውስጥም ሆነ ከሌላ ቦታ አመንጭተው ሊፈጥሩ አይችሉም። ይህንን የትኛውም ሰው አይችልም። እርስዎ ማድረግ የሚችሉት የገዛ ራስዎን ኃይል ነፃ ማድረግ መልቀቅ፣ መለወጥ፣ ማጋራት ነው። አንድ ሰው ተጨማሪ ሳያሻው ከበቂ ኃይል ጋር ተወልዷል። አንዳንድ ግዜ ኃይልን እየጨመሩ እንደሆነ ሊሰማዎት ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን አይደለም። ነባሩን ኃይልዎን ለቀቅ ነው ያደረጉት።

ይህም ነጭ ጋዝ ላይ ክብሪት እንደመጫር ወይም በማራገብ የተዳፈነውን እሳት የማንቦግቦግ የመሰለ ነው። አንዳንድ ሰዎች ኃይል እንደሚያንሳቸው ይሰማቸዋል። ሐቁ ግን በኃይል የተሞሉና ውስጣቸው የተጋደመ፣ ክብሪቱ የሚጠብቅ ወይም አቅጣጫና ምሪት የሚጠባበቅ ኃይል የተትረፈረፋቸው መሆኑ ነው። በመሰረቱ አንድ ሰው ጥቅም ላይ የሚያውለው ኃይል ግለሰቡ በራሱ ባለው ጥቅም ላይ የማዋል ፍላጎት መጠን የሚወስን ነው። ኃይሉን የሚነዝረውና እጥቅም ላይ የሚያውለው የፍላጎት መጠኑ ነው። ጠንካራ ፍላጎት በበርካታ ኃይል እንዲለቀቅ ያደርጋል። ተጨማሪ ኃይል ከፊተኛው በሚልቅ የፍላጎት ግለት አማካኝነት የሚለቀቅ ነው። ያለ ፍላጎት ኃይል ፍሬ ቢስ ሆኖ ይሸፈናል።

ማንም ሰው የመከወን የጋለ ፍላጎት እስካልኖረው ድረስ ኃይሉን ጥቅም ላይ ሊያውል አይችልም። ለመከወን መሸቀዳደም ብቻ የተፈጥሮ የሆነውን ውስጣዊውን ኃይል የተለቀቀ ያደርገዋል። ይሁን እንጂ ግልፅ ያልሆነና ጥልቅ ምኞት ከፍላጎት ጋር መምታታት የለበትም። ትክክለኛ ፍላጎት የተብራራና የሚገለጽ ነው። ለምሳሌ መጨነቅ ፍላጎትን የሚጠቁምና ኃይልን አነሳሽ ቢሆንም ያ ግን ቅጣትና ምንም ምህረት የሌለው ባርነት ነው››

ከዚህ መረዳት የምንችለው እውነታ የሠው አእምሮ ምንም ገደብ የሌለውና ዳርቻ ያልተበጀለት ሆኖ ሳለ ውስጣችን የተንጋለለውን ብቃት አፍልቀን እርግጥ ማን እንደሆንን ለማወቅና መሆን የምንሻውን ለመሆን ራሳችንን መገፋፋት እንዲሁም መለጠጥ እንዳለብን ነው።

BOOKSITE
BOOK STORE



የኛ ሰው በባህር

ልዑል ብርሃነመስቀል - ማሪን ኦፊሰር
በሊንዳ ሺፒንግ ኢንተርናሽናል፣ ኤሜሬትስ

ከ1960ዎቹ ጀምሮ በባህር ህይወት ያሳለፉ ከዛም ወደ መካከለኛው ምስራቅ አካባቢ እና በመላው አለም በብዛት ተቀጥረው የሰሩ ኢትዮጵያውያን ባህርተኞች የሙያ ብቃታቸው እና የስራ ዲሲፕሊናቸው መለኪያ ሆኖ በሄድንበት ሁሉ መልካም አቀባበል እንዲገጥመን መንገድ የከፈቱልንን ብዙ የሙያው ሰዎች እያሉ እኔ ይህን ፅሁፍ ማዘጋጀቴ ድፍረት ቢሆንም ከምንም ይሻላል እና አፍጥቼ ይቺን ብያለሁ። ከደርግ ባህርተኞች እና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ለራሱ መልምሎ ውጪ ሀገርም ሀገር ውስጥም ለአመታት አሰልጥኖ ካሰማራቸው ጥቂቶች ውጪ አብዛኞቻችን እንጀራ ፍለጋ ወደባህርተኝነት ህይወት ስንገባ ሀይቅ ላይ ሰልጥነን ነው። ከባድ የጥንቃቄ ስልጠናዎችን ወስደህ የምትጀምረው ስራው ምን ያህል አደጋ የበዛበት እንደሆነ ምልክት ቢሆንም ወደ ስራው ሲገባ ያሉትን ነገሮች (መጥፎ አየር፣ ከተለያየ ሀገር ሰው ጋ በባህሪና በስራ ተግባብቶ መኖር፣ የምትሰማቸውና የምታያቸው አደጋዎች) ምን ያህል ጥንቃቄ እና የሙያ ብቃት እንደሚያስፈልግህ ያሳዩሀል።

ባህርተኛን በሄደበት የሚከተሉት ስሞችም መሰረተቢስ ናቸው ማለት ይከብዳል የቤተሰቡን ናፍቆት እና የፍቅረኛውን ናፍቆት ለማስታገስ በዙሪያው ካለው ሰው ጋር በቤተሰብ መንፈስ ሲጨዋወት ይከርማል ። አብዛኛው ሰው ባህር ላይ ሀይማኖተኛ መሆኑ ይገርማል ። ምናልባት ውሀ ላይ ስትሆን ምን ያህል ትንሽ መሆንህን ስለምትረዳም ይሆናል ። በደራሲ አይን ቢታዩ እና ቢፃፉ የሚያስብሉ ነፍስ የሚሰርቁ እንደ ፀሀይ ስትገባ እና ስትወጣ ያሉ ትዕይንቶች፣ ጥርት ያለ ሰማይ ላይ ጨረቃ አምሮባት ማየቱ እና ወጀብ እና ነፋሳት ፣ መርከብ ተከትለው የሚፈነጩ የባህር ውስጥ እንሰሳት በለሊት ባህር ላይ ለስለስ ያለ ንፋስ እና ምርጥ እይታዎች እርካታ ከሚሰጡት እና እንኳን ይሄን ሙያ መረጥኩ ከሚያስብሉ ብዙ ነገሮች መሀል ናቸው።

በባህረኛ ህይወት ውስጥ የስራ ሰአት ማክበር ላይ ቀልድ የለም! ቢያምህ መድሀኒት ወስደህ ወደስራ እንጂ መተኛት አይታሰብም (ባህር ላይ ከሆንክ) ስራውን አንድ ሰው በአግባቡ ባለመስራቱ ብቻ ሊደርስ የሚችለው አደጋ ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው ንብረቶች እና መርከብ ላይ ብቻ ሳይሆን በሰራተኞች ህይወት ጭምር ስለሆነ ሁሉም ሀላፊነቱን በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ግዜውን በስርአት በመጠቀም ሊፈፅም ግድ ነው። ንፅህናን መጠበቅ በቁጥር ብዙ ከሆኑ ሰዎች በጋራ ለቀናት ሲበዛም ለወራት አንድ ላይ በሚቆዩበት ቦታ ግዴታ እንጂ ምርጫ አይደለም።

በየቀኑ ሁሉም ሰው መርከብ ላይ ሲሰራ ትምህርት ላይም ነው የመርከብ ወለል ላይ ወይም የመርከቡ ከፍተኛው አካባቢ የሚሰራ ሰው ከታችኞዎቹ ስራዎች መጥፎ አየርን በጥንቃቄ አጥንቶ መርከቧን እስከመንዳት ድረስ የሚማረው፣ engine room ያለውም ከትንሹ ስራ በአስቸጋሪ ቦታ እና ሁኔታ ውስጥ ሞተር እና ጄነሬተሮችን እየጠገነ እና ጤንነታቸው እየጠበቀ ማቆየትን የሚማረው በስራ ላይ ነው። እራስን ለማሳደግ እና ተጨማሪ ኮርሶች ወስዶ ብቁ ለመሆንም የባህር ላይ ልምድ ግዴታ ያስፈልጋል።

ከተለያዩ ሀገር ዜጎች ጋር በምታሳልፈው የስራ ግዜ እና አብሮ በመኖር ምታገኘው የህይወት ልምድም ቀላል አይባልም (እኔ እንኳን በዚች አጭር ግዜ ከህንዶች፣ ፓኪስታን፣ ፍሊፒን፣ ጋና፣ ኢንዶኔዥያ፣ ስሪላንካ፣ ታንዛኒያ፣ ባንጋሊ፣ እና ከሀገሬ ልጆች ጋር የመስራት እድል ገጥሞኛል። ለእንደኔ አይነቱ በተፈጥሮ የተሰጠው መኖሪያ እስኪመስል ከነ አደጋዎቹ ስራው ቢመችም የመርከበኛ ህይወት እና የባህር ላይ ስራ ለአብዛኛው ሰው ሚሆን ስራ አይደለም። የመርከብ ህይወትን ለምዶ ለመኖር ብቸኝነትን መቻል ከብዙ እና ከተለያዩ ሰዎች ባህሪ ጋር ተቻችሎ መኖር ከተለያዩ አየር ሁኔታዎች እና የአመጋገብ ስርአቶች ጋር የመላመድ ብቃት የግድ ሚያስፈልጉ የግል ባህሪያት ናቸው።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ የመጀመሪያ ድግሪዋን፣ ከዛው ዮኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋና መስማት የተሳናቸው ባህል ሌላ ዲግሪ እና - ከኦስሎ ዩኒቨርስቲ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ዘርፍ ሁለተኛ ዲግሪዋን ሰርታለች። የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች ብሄራዊ ማህበር መስራች ***መዓዛ መላኩ*** *የዛሬ እንግዳችን ናት።*

1) መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር ለመግባባት የሚያስችሉ ትምህርቶችን ወስደሽ እነዚህን የህብረተሰቡን ክፍሎች ለማገዝ ምን አነሳሳሽ?

-መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር ለመስራት (ለመግባባት) የመጀመሪያው ነገር ሰዎቹን ለመርዳትና ለመረዳት መፈለግ ነው። መርዳት ከሚሰጠው እርካታ በተጨማሪ የማታውቀውን አንድ የቋንቋ ክህሎትን ይጨምርልሃል፣ የቤተክርስቲያን አገልግሎትን ለነሱ ተደራሽ ለማድረግ በመፈለግ ቋንቋውን ተማርኩ። ሲገባኝ ግን ከነሱ ጋር መስራት ብዙ ሰዎች የማይደፍሩት ግን ደግሞ ጥሩ አማራጭ ሆኖ ስላገኘሁት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ስልጠና ወስጄበታለሁ።

2) አሁን ያለንበት ዘመን የቴክኖሎጂ ከመሆኑ አንፃር ዲጂታሉ አለም ለነዚህ የህብረተሰቡ ክፍሎች ያመጣው ጥቅም ምንድነው? አሰቸጋሪ ሁኔታስ አለው? በአጠቃላይ መስማት የተሳናቸው ሰዎች በዚህ የዲጂታል ዘመን እንዴት ነው እየኖሩ ያሉት?

-በቀላሉ እንደምንረዳው ያለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን ከቴክኖሎጂው እድገት ጋር መወዳደር (ራሳቸውን ማዘመን) ነው። ዲጂታሉ አለም በተለይ ድምፅን (የንግግር ቋንቋን) ወደ ምልክት ቋንቋ የመቀየር እና መረጃን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር መስማት ለተሳናቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች መልካም አጋጣሚዎችን ፈጥሯል፣ በሌሎች ሰዎች ላይ ጥገኛ እንዳይሆኑ ነገሮችን ቀላል አድርጎላቸዋል። ሆኖም እንዲህ ያሉ መሰል ቴክኖሎጂዎች የገንዘብ አቅምን የሚይቁ በመሆናቸው ለእኛ ማህበረሰብ ሩቅ ናቸው። ሆኖም የትምህርት እድል ያገኙ መስማት የተሳናቸው ዜጎች በቀላል የጽሁፍ መረጃዎችን ማግኘትና ራሳቸውን የማብቃት እድሉ አላቸው።

3) ሌላው ማህበረሰብ መስማት ስለተሳናቸው ሰዎች ሊያውቃቸው የሚገቡ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

መስማት መሳን እንደ ማየት መሳን ወይንም የእንቅስቃሴ እክል የሚታይ አይነት የአካል ጉዳት አይደለም፣ መስማት መሳን የድምፅ (የልሳን ቋንቋን) መስማት አለመቻል ነው። ይህ ነገር በማንኛውም እድሜ ሊከሰት የሚችል ሲሆን ሙሉ ለሙሉ ካለመስማት ጀምሮ የተለያዩ ደረጃዎች አሉት፣ የምልክት ቋንቋ መስማት የተሳናቸው ሰዎች ዋነኛነት የሚግባቡበት ቋንቋ ሲሆን እንደ ሀገሩ ይለያያል ። ይህ ማለት ዓለማቀፋዊ ቋንቋ አይደለም።

4) መስማት የተሳናቸው ሰዎች በብዛት የሚሰማሩባቸው የሙያ ዘርፎችስ የትኞቹ ናቸው?

መስማት የተሳናቸው ሰዎች ቴክኖሎጂን ውይንም ምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችን ተጠቅመው የተለያዩ የሙያ ዘርፎች ላይ ስኬትን ማስመዝገብ እንደሚችሉ ብዙ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል። ሆኖም የንግግር ቋንቋን መቻል ግድ የሚሏቸው - እንደ የዜማ ድርሰት አይነት የስራ ዘርፎች ላይ ሊሰማሩ አይችሉም።

5) መስማት የተሳናቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማገዝ ማህበረሰቡ ምን ማድረግ አለበት?

መስማት የተሳናቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ ለቋንቋው ሙሉ እውቅና መስጠት ነው። ይህ ሲሆን ትምህርት ቤቶች ላይ በስፋት አገልግሎት ላይ እንዲውል፣ ፍርድ ቤቶች እንደማንኛውም ቋንቋ አስተርጓሚዎችን እንዲያዘጋጁ፣ የመገናኛ ብዙሃን መገልገያ እንዲሆን፣ ተገልጋዮች በቋንቋቸው የትኛውም ቦታ አገልግሎት እንዲያገኙ መጠየቅ ይችላሉ።

መስማት መሳን የማይታይ አካል ጉዳት እንደመሆኑ በየትኛውም እንቅስቃሴ መስማት የማይችል ሰው መኖሩን ማስታወስ ይገባል። አንድ ሹፌር የመኪናውን ጡሩንባ ድምፅ ሰምቶ ከመንገዱ የማይርቅ ወገን መኖሩን፣ ያወራነውን ሁሉም እንደማይሰማንም ማስታወስ አለብን። በፅሁፍ መግባባት ለጥቂቶች መስማት የተሳናቸውም የመግባቢያ አማራጭ ነው።



የመፅሃፍት ጥቆማ

ስለ ትናንሽ አለላዎች

በስምኦን ሩፋኤል

የትናንሽ አለላዎች ደራሲ ዶ/ር ዮናስ አ. የመፅሃፉን በር ሲከፍት ‘ሰው ትናንቱ ነው!’ በሚል ብያኔ ይጀምራል። ደራሲው ትውስታ ካለፈው ህይወት ጓዳችን እንደሰበዝ እየመዘዝን ባሻን ጊዜ የምናሰላስለው የትዝታ አለላ እንደሆነ በተሰናሰሉ ትርክቶቹ አዋዝቶ ብያኔውን እንድንፈትሸው መደላድል ሰጥቶናል።

በእርግጥም ሰው ስላለፈው ህይወቱ አንዳችም ትዝታ ባይኖረው የሰውነቱ ጣዕም ምኑ ላይ ይሆን ነበር ? ለዛም ነው ደራሲውም ‘ሰው ከነገው የትናንቱን የሚናፍቀው ለምንድን ነው?’ ብሎ በጥያቄ የሚሞግተን (ገፅ 48) ::

ትናንት የሰውነት ውሀ ልክ ነው ፤ የኑሮ ውደታችንም በጊዜ ላይ ተሳፍሮ በህይወት እና በሞት መካከል እየተሸከረከረ የትናንታችን ዱካዎች በመከተል ዛሬያችንን እና ነጋችንን ይፀንሳል። ዛሬም ነገም መልሰው ትናንትን ይፀንሳሉ። ሽክርክሪቱ ይቀጥላል! በመጀመሪያ ትናንት ነበር። ትናንትም ከዛሬ ጋር ነበር። ትናንት- ዛሬንም ነገንም- ሆነ! ደራሲውም “ትናንት የሆነው ዛሬ ደግሞ ይሆናል ። ማለት ክብነት አለው የኢትዮጵያዊ ህይወቱ። ይነሳል-ይወድቃል፣ ያገኛል-ያጣል፣ ይከብራል-ይዋረዳል፣ ይበለፅጋል-ይደኸያል፣ ይኖራል-ይሞታል...ይህ የአዱቱ ግማሽ ነው። ዙር ይሞላና ከጀመርንበት እንጨርሳለን።” እንዲል (ገፅ 102)

የትዝታ አለላዎች በህይወትና በሞት መካከል የተነጠፉትን የትናንት ዱካዎች ተሸክመው የሞትን አድማስ ተሻግረው በነዋሪው ልብ ውስጥ ህልውናችን የሚተክሉ ሰንደቆች ናቸው። ደራሲው “የሚያስታውሰው የሌለ ነገር ሁሉ ይሞታል።

የምንሞተው፤ ህያው የምንሆነው በምንተወው የትዝታ ዱካ ነው።” እንዲል (ገፅ 65)

በመጨረሻም ከመፅሃፉ

“ምክንያት አልባ ለሆኑ ነገሮች ምክንያት ለመፈለግ መፈለግ አድካሚ አይደለም፣ የሚከብደው ምክንያት ለማግኘት መፈለግ ነው። ሁሉም ለኑሮውና ለሞቱ ምክንያት ፋለጋ ይባክናል። ዕድሜ ልኩን ምክንያት አልባ ለሆኑ ነገሮች ምክንያት ሲያበጅ ነው የኖረው። ፈልገን ስናጣ የየራሳችንን እውነት እንፈጥራለን። በህይወት ለመቆየት የሚደረግ ጥረት ነው። አንጎላችን አንጎላችንን መሸወዱ አይገርምም?” (ገፅ 119) የዶክተር ዮናስ አ . የበኩር ስራ የሆነውን ስለትንንሽ አለላዎች አጣጥመንዋል! ለዳግማዊው ያብቃን! ምስጋና ለደራሲው!

የመፅሃፉ ዋጋ 100 ብር ሲሆን ጃዕፈር እና ሊትማን መፅሃፍት ቤቶች እና ሮማናት አሳታሚ እና አከፋፋይ ጋር ማግኘት ይቻላል ::

ባህላዊ ቅኝት

የጋሞ ማህበረሰብ

በፈለቀ ኮንታሞ

የጋሞ ብሔር በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኝ ሲሆን በምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ጥንታዊ ሥልጣኔ ስለመሆኑ አስረጂ የሚሆኑ ሺህ ዘመን ያስቆጠሩ በደጋ ኦሞ የሚገኙ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች፤ የድንጋይ ቅርፃ ቅርፆች፤ ጥንታዊ የሊሻ መንዴር፤ በጋንታ፤ ኦሞ፤ ኦቾሎ፤ ዶረዜ የሚገኙ ጥንታዊ ሸመና ሥፍራዎች ከብዙ ጥቂት ስለ ብሔረሰቡ በስፋት ሊያስረዱ የሚችሉ የአርኪዮሎጂ ሳይቶች ናቸዉ።

ጋሞ ከጥንት ጀምሮ ነባር የጥጥ ዝሪያዎችን አምርቶ፤ የምያመርተዉን ጥጥ ፈትሎ የተለያዩ አልባሳትን ሰርቶ የሚለብስና ለሌሎችም የሚያለብስ ነዉ። የጋሞ ብሔረሰብ መኖሪያ 19ኛዉ መቶ ክ ዘመን መጨረሻ ድረስ የራሱ የሆነ ባህላዊ አስተዳደር መዋቅር የነበረው እና ዛሬም ድረስ ይህንኑ ከዘመናዊ አስተዳደር ጋር በማዋሃድ ልማዳዊ ወግና አሰራሪ ጠብቆ በመተሳሰብ በመፈቃቀር ከተራ እስከ ከባድ ግጭት እንኳን ቢፈጠር በአደባባይ /ዱቡሻ/ በመሰባሰብ ችግሮችን በዉይይት በመፍታት ላይ ይገኛል። ብሔረሰቡ በ 1999 ዓ.ም በተደረገዉ በህዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት 1,107,163 ሲሆን አጠቃላይ ቆዳ ሽፋኑ 7,366.59 ስኴር ኪ/ሜትር ነዉ።

የጋሞ ተፈጥሮአዊ መልካ ዓምድር ተራራ የበዛበት እና አብዛኛዉ ደጋና ወይና ደጋ የአየር ንብረት ያጠቃልላል።

በደጋዉና ወይና ደጋዉ ገብስ ፣ ጥራጥሬ፣ ቅመማ ቅመም ወዘተ በማምረት የሚተዳደሩ ሲሆን የቆላዉ ደግሞ ጥጥ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ጤፍ፣ ቅመማ ቅመም በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በአገራችን ግንባር ቀደም ነዉ። የጋሞ ሰንሰለታማ ተራራ 100 ኪ/ሜትር ሜትር በላይ የሚረዝም ሲሆን በዙሪያዉም ብዙ ሕዝብ ለሸህ ዓመታት ተጠጋግቶ ሠፍሮ ይገኝበታል ።የታላቁ ስምጥ ሸለቆ ሐይቆች መጋቢ ወንዞችም መነሻ ነዉ።

ይህ ተራራ በባህላዊ መንገድ ይጠበቃል። በተራራዉ ዙሪያ ያሉ ነዋሪዎች በተራራዉ ከሚሰማሩ እንስሳት ፍግ በመጠቀም በዋናነት በገብስና በድንች ምርት ይታወቃሉ።

ልዩ ሀሳብ እንጂ ጠላት የለም

መኮንን ከተማ ይፍሩ - ጆርጅ ታውን ዮኒቨርስቲ

ፈረንጆች እንደሚሉት "You are either with me or against me" "ወዳጄ ነህ ካልሆነ ግን ጠላቴ ነህ" ሆኗል የኛ ነገር። የሰው ልጅ ሁሉም ነገር ላይ መስማማት አይችልም። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በምን መንገድ መሄድ አለባት? በሚለው ጉዳይ ዙሪያ ብዙ ልዩ ሀሳቦች ይኖራሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ ሀሳባችንን የማይደግፉ ሰዎች ልዩ ሀሳብ እንዳላቸው መቀበል እንጂ ጠላቶቻችን አድርገን መፈረጅ የለብንም። ግትር የሆነውን የፖለቲካ ባህላችንን እንቀይር !! ምክንያቱም ሀገር ያፈርሳል!!

ልጅ እያለሁ ትዝ የሚለኝ ነገር ቢኖር ልዩ ሀሳብ ያላቸው ሁሉ ፀረ አብዮተኛ ተብለው ይፈረጁ እንደነበረ ነው ። በሚቀጥለው መንግስት ደግሞ የድሮ ስርዓት ናፋቂ ተባሉ። አሁን ደግሞ የለውጡን ሂደት ያልተቀበሉ ወይም የማይደግፉ ይባላሉ። ሀሳቦቻችንን የማይቀበሉትን ሰዎች ብዙ ስሞችንም ሰጥተናል። አደሃሪ ፊውዳል ፀረ አብዮተኛ ኢምፔርያሊስት ነፍጠኛ ጠባብ ወዘተ...። ባጭሩ ፈረንጆች እንደሚሉት "You are either with me or against me" " ወዳጄ ነህ ካልሆነ ግን ጠላቴ ነህ" ማለት ነው። እኔ እንደሚገባኝ ልዩ ሀሳብ እንጂ ጠላት የለም።

ሀገራችን ያፈራቻቸው ብዙዎቹ ቅን ምሁራኞችና ሽማግሌዎች በሀገራቸው ፖለቲካ የማይሳተፉበት አንደኛውም ምክንያት ይሄው ነው። አንዱ ጥቁር ነው ሲል ሌላው ነጭ ብሎ ሲከራከር በምሁራንና በሽማግሌዎቻችን አለም ውስጥ ሁሉም ነገር ጥቁርና ነጭ ሆኖ አይታይም። ሌሎቻችን የማይታየንን በጥቁሩና በነጩ መካለል ያለው ግራጫ ጎልቶ ይታያቸዋል። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ግን የሚያስተናግደው ሀሳብ ጥቁር ወይም ነጭን ስለሆነ ግራጫን የሚያዩትን ኢትዮጵያኞች ቦታ ሊሰጣቸው አልቻለም። ድሮ መሃል ሰፋሪ ይባሉ ነበር። ዛሬ ደግሞ ምን ብለናቸው ይሆን?

ያለንበትን ችግር እናውቀዋለን። እዚህ ያመጣንም ምን እንደሆነ እናውቀዋለን። ይሄ ግትር የሆነ ጥቁር ነው ወይም ነጭ ነው የሚለው የፖለቲካ አስተሳሰብ መቀየር አለበት። ኢትዮጵያ የብዙ ልጆች እናት ናት። አንዱ ከሌላው የበለጠ ሊያስብላት አይችልም። ሁሉም ልጆችዋ እኩል ነው የሚያስቡላታ ብዬ አምናለሁ። ሀሳቦቻችንና አካሄዳችን ግን ልዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ጠላቶች ግን ሊያደርጉን አይችሉም።

You are either with me or against me" "ወዳጄ ነህ ካልሆነ ግን ጠላቴ ነህ" ማለት አቁመን ወንድምና እህቶቻችን ያላቸውን ሀሳብ እናዳምጥ። ሀሳባቸው ከእኛም ሊበልጥ ይችላል። ተወያይተንም አስታራቂ ሀሳብ ማምጣት እንችል ይሆናል። በመደማመጥ ብቻ ነው ምናውቀው።

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!

የታባቱ ሞትም ይሙት

(ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን)

እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ስሞት ሞትም
አብሮኝ ይሙት
በሳቅ በደስታ ግደሉት
በሃሴት በዕልልታ ውገሩት፤
እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ለሞት የልብ ልብ
አትስጡት
ናቁት አጥላሉት አውግዙት
በሙሾ ግነን አትበሉት
በሞቴ፣ እንዳታስደስቱት።
እንደ ዶርዜ ወንድሞቼ
በሳቅ ታጅቤ ኮርቼ
ሞቴን በዘፈን ሞልቼ
በዳንኪራ ሰበቃና፣ በዘፈን ሆይታ አካትቼ
በሠርጌ ብቀበር ሞቼ
እፀድቅ ነበር ባትረሱ
በእንባ ውሌን ባታፈርሱ።

እባካችሁ ዘመዶቼ፣ በሳቅ ጉዞ ፍታት
ፍቱኝ
በሙሾ ዋይታ አታጅሉኝ፤
እናቴም ፊትሽ አይክሰል
በእልልታ ብርሃን ይንበልበል፤
በእረፍቴ እንዳታፌዝብኝ
በሠርጌ እንዳታለቅሽብኝ።

ገጽሽ በጭንቅ አይወረስ
ልብሽ በጎዘን አይላበስ
በሆድሽ ሞት አይፀነስ
ዕንባ በአይንሽ አይቋጠር
የሞት ቅስሙ እንዲሰበር።

አዎን፣ አደራ፣ አደራችሁ፣ የሙት ውሌን
ተቀበሉኝ
ደስታዬን ተካፈሉኝ
ለንስሃ ሞት አይደለም፣ ለፍሠሐ እረፍት
አብቁኝ፤
ደስታዬን ተካፈሉኝ
ለንስሃ ሞት አይደለም፣ ለፍሠሐ እረፍት
አብቁኝ፤
በዶርዜ እስክስታ አስቀብሩኝ
በእልልታው ጉዞ አሳጅቡኝ
በጦሩ ችቦ አሳጥሩኝ፤

ጭብጨባችሁ በስልቱ ይውረድ
ዛፍ ቅጠሉም አብሮ እስኪረግድ፤
ሀገር ምድሩም ያቅራራ
ሀሴት ነው ይበል፣ ጀቢራ
ሠርጌ ነው፣ ይምታ ዳንኪራ
እንዲህ ስሜት ሲፍለቀለቅ፣ ሲፈነድቅ
ሲግል ሃሞት
ቱማታው ሲዋጥ በላቦት
ሆይታ በሆይታ ሲራኮት
ማሳለፊያ መግቢያ ሲያጣ፣ ፍርሃት
ገበናው ሲራቆት መቃረቢያ ፍንጭ
ሲያጣ፣ በእልልታ ሲወገር ብሶት…
ብቻ ነው፣ ሞት እራሱ የሚሞት።

እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ሞትም አብሮኝ
ይሙት!
በእልልታችሁ ግደሉት
በዳንኪራችሁ ዉገሩት
ከአጥንቴ በታች ቅበሩት።

(ዶርዜ ሰፈር – 1963 ዓ.ም.)



ነገረ-ሕግጋት

ሰማንያ- ሲታሠር

(በካፒታል ክብረ - የህግ ባለሞያ እና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የህግ አማካሪ)

በ1992 ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 213/1992 መሰረት ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት እና ንብረት ላይ የሚከተሉትን ውጤቶችን ያስከትላል።

-ተጋቢዎች እርስ በእርስ የመከባበር ፣ የመተጋገዝ እና የመደጋገፍ ግዴታ በህግ ተጥሎባቸዋል። ቤተሰብን የመምራት እኩል መብት ለባልና ለሚስት በህግ ተሰጥቷል። ከባልና ከሚስት አንደኛው ችሎታ ያጣ ፣ የጠፋ ወይም ቤተሰቡን ጥሎ የሄደ እንደሆነ ወይም ከመኖሪያ ስፍራው በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌ ምክንያት ፈቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ በሚገኝበት ጊዜ የቤተሰብ አመራርን አንደኛው ተጋቢ ብቻውን ይፈጽማል።

ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ እንዲሁም ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር መደበኛ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ በህግ ግዴታ ጥሎባቸዋል። የሚኖሩበትን ሥፍራ በጋራ ይወስናሉ።

<u>ጋብቻ የተጋቢዎቹን ንብረት በተመለተ የሚኖረው ውጤት</u>

-ተጋቢዎች ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ወይም እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት እለት በውል መወሰን ይችላሉ።

-ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው ይቀራሉ።

-ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሽጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል።

- ባልና ሚስት ከጋብቻ በኋላ ከግል ጥረታቸው እና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ።
- አንደኛው ተጋቢ የግል ሃብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል።

- ተቃራኒ የተጋቢዎቹ ስምምነት ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሌለ በስተቀር ባልና ሚስት በየግል የሚያገኙት ገቢን ራሳቸው ይቀበላሉ ፣ የባንክ አካውንት ከፍተው በየራሳቸው ያስቀምጣሉ ሆኖም በተጋቢያቸው ሲጠየቁ የገቢ መጠን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

ወደ ገፅ 17 ይዞራል

ግንቦትን በታሪክ

በደቻሳ አንጌቻ (የቀድሞ አብዬታዊ ሰራዊት ድረ - ገፅ መሰራች)

በቀረብኝ ኖሮ ለምን በላሁት
አያበቅለው የለ ሰኔና ግንቦት
የግንቦቱ ባሰ አረም በዝቶበት

ግንቦት ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ተወለዱ ። ግንቦት 1 ደግሞ ኢህአዴግ ሊቀመንበርና የኢትዮጵያ ጠ/ሚ የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ የተወለዱበት እለት ነች።

ግንቦት 8/1981 ዓ.ም አዲስ አበባና አሥመራ ላይ በከፍተኛ ጀነራል መኮንኖች የተሞከረው መፈንቅለ መንግስት የከሸፈበት እለት ነበር ።

ግንቦት 10/1981 ዓ.ም በአሥመራ የተሞከረውና የ 3 ቀናት እድሜ ያስቆጠረው መፈንቅለ መንግስት በ102ኛ አየር ወለድ ክ/ጦር አባላት የከሸፈበት እለት ነበር ።
ግንቦት 11/1982 ዓ.ም በመፈንቅለ መንግስቱ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የነበሩት የእንግሊዙ ብሪቲሹ ሳህድረስት ሮያል ሚሊተሪ አካዳሚ ምሩቅ የነበሩት ምጡቁ ብ/ጀ ተስፋዬ ትርፌ ጨምሮ 12 ጀነራል መኮንኖች በፖለቲካዊ ውሳኔ በግፍ የተረሸኑበት አሳዛኝ ቀን ነበር ።

ግንቦት 13/1983 ዓ.ም ለ17 አመታት ኢትዮጵያን የመሩት የሪፐብሊኩ ፕሬዚደንት ፣ የኢሰፓ ሊቀመንበር ፣ የአብዮታዊው ጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ብላቴ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ተቋም ለመጎብኘት ብለው በኬንያ አድርገው ወደ ዙምባቡዌ የሄዱበት እለት ነበር ።

ግንቦት 10/1983 ዓ.ም በደርግ ,EPLF ,TPLF/ EPRDF እና OLF ከፍተኛ አመራርና ተወካዮች መካከል በአሜሪካዊው ከፍተኛ ዲፕሎማት ሚስተር ሄርማን ኮሄን አማካይነት በእግሊዝ ለንደን የይስሙላ ድርድር ለማካሄድ የተሞከረበት ውጤት የለሹ የለንደን ኮንፈረንስ የተካሄደበት እለት ነበር ።

ግንቦት 16/1983 ዓ.ም ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመነጠል ለድፍን 30 አመታት የትጥቅ ትግል ሲያካሂድ የነበረው የኤርትራ ነፃ አውጪው ድርጅት / ሻእቢያ አሥመራን ከሁለተኛው አብዮታዊው ሰራዊት ጋር ተደራድሮ ያለምንም ጦርነት የተቆጣጠረበትና የደርግ አስተዳደር በኤርትራ ክ/ሀገር ያበቃበት እለት ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል ።

ግንቦት 20 /1983 ዓ.ም ኢህአዴግ ዋና ከተማዋን አዲስ አበባን በመያዝ የሚኒልክ ቤተመንግስትን ተቆጣጥሮ ኢትዮጵያን ለ27 አመታት ለመምራት እድል ያገኘበት እለት ነበረች ።

ሰማንያ- ሲታሠር ከገፅ 16 የዞረ

- ባልና ሚስት የጋራ ሃብታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ። በተጋቢዎቹ ስምምነት፣ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ወይም በማናቸው ምክንያት አንደኛው ተጋቢ ብቻ የጋራ ሀብት አስተዳዳሪ ሲሆን ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ሃላፊነት ይኖርበታል።

-በተጋቢዎቹ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ለሌሎች ሰዎች መብት ለመስጠት የሚደረግ ስምምነት፣ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) በላይ ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች በማናቸውም መልኩ ለማስተላላፍ የሚደረግ ስምምነት፣ ብር 100 (መቶ ብር) በላይ ያለውን ንብረት በስጦታ ለማስተላለፍ የሚደረግ ስምምነት እና ብር 500 (አምስት መቶ ብር) በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር የሚደረግ ስምምነት የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው።

-ተጋቢዎች የትዳራቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸው እና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።

ደርሼ ተመለስኩ!!

(ፀሐይ መላኩ - የመጀሪያዋ ሴት የረጅም ልብ ወለድ ደራሲ)

የኮሮና ወጀብ ጠልፎኝ ጥቂት መንገድ ወስዶኝ ነበር።
በሥቃዩ አዙሪት ውስጥ ገብቼ መከራውን ቀምሻለሁ። ሥቃዩ እጅግ አስጨናቂና ከባድ ነው።በዚህ ውስጥ ሆኜ አምላኬን ተማፀንኩት። እሱም በጽኑ ክንዱ ስቦ አወጣኝ። ለዘላለም ይመስገን።
ውድ ወገኖቼ፣
ይህንን የቸነፈር ጊዜ ለመሻገር፣ ከምሁራን የሚሰጠውን ቅን ሀሳብና ምክር ልንቀበልና ልንጠነቀቅበት ይገባል። መኖርን ለመኖር ተጠንቅቃችሁና ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ተብለናልና።
ከወጀቡ ይጠብቃችሁ።

- አፍና አፍንጫችንን በአግባቡ እንሸፍን ።
- ባልታጠበ እጅ አይን ፣ አፍንጫ እና አፍን ከመንካት እንቆጠብ ።
- እጃችንን በአግባቡ እንታጠብ ።
- ውሃ በማይገኝበት ቦታ ሳኒታይዘር እንጠቀም ።
- አካላዊ ርቀታችንን እንጠብቅ።

የጤና ባለሞያዎች የሚሰጡንን ምክር በመስማት እና በመተግበር ራሳችንን እና ሌሎችን ከኮሮና ቫይረስ እንከላከል ።
በእኔ የደረሰ አይድረስባችሁ !!

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አጠቃላይ የኮቪድ ማሳያ ሰንጠረዥ

የወሩ ምርጥ ፊልሞች



1) The Manchurian Candidate (2004)
Gener drama mystery sci. fiction
Rating 6.6 /10

2) Election (1999)
Gener comedy , drama , romance
Rating 7.2/10

3)Head of State (2003)
Gener comedy
Rating 5.5 /10



4)The Candidate (1972)
gener comedy , drama
rating 7/10



5) All the President's Men (1976)
gener : - biography , drama , history
rating 7 /10

6) In the Line of Fire (1993)
gener :- action , crime , drama
rating 7.2/10

እነዚህን እና ሌሎችም የአሜሪካንን ፕሬዝደንሻል ምርጫ ላይ ያተኮረ
ፊልሞችን - በቴሮይስ የፊልም ማዕከላት በስድስቱም ቅርንጫፎች ማግኘት ይችላሉ::

Trios
Movie Center
0911 839797, 0920 848711

www.bet24.et

ላይ በመሄድ አካውንት ሲከፍቱ የ10 ብር ስጦታ ያገኛሉ

Go to www.bet24.et
& register to get 10 birr welcome bonus now

Join our telegram channel now
https://t.me/bet24Ethiopia
Call us anytime for questions

+251 - 903 500 - 000



Demera Media & Communication Service PLC
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
+251 911 057837 +251 911 488888

አሉላ ዮሐንስ ማስታወቂያ

የመመረቂያ መፅሄቶች፣ የአንዋል ሪፖርቶች፣ ወርሃዊ መፅሔቶች፣ የድርጅት ካታሎጎችን
ከማዘጋጀት እስከ ህትመት ጥራታቸውን በጠበቀ ሆኔታ አትመን በሰአቱ እናስረክባለን።

0911 871767